# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን የመደመር ምንጭ ናት።

**መስከረም 14 ቀን 2012 ዓ/ ም**

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**
**nigatuasteraye@gmail.com**

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን እኛ ኢትዮጵያውያን በመደመር ኅብር እንድንሆን የተጠቀመችባቸው **ሁለገብ መስተጻምራት፡-**

የቀደሙ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አባቶች የመደመርን ጽንሰ ሀሳብ እንዴት ይመለከቱት ነበር? ተብሎ በድያስፖራው ለተነሳው ጥያቄ፤ ከሞላ ጎደል ለመመለስ መጀመሪያ ጳጉሜ 2ሽ 10 ዓ/ም በኢትዮጵያ ኤምባሲ ዋሽንግተን ዲሲ አዳራሽ ይህ ጦማር ቀረቧል ። እንደገና ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ/ ም አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ስብሰባ ቀርቧል። ለቤተ ክርስቲያናችንም ሊቃውንት ጉባዔና ለሚመለከታቸው ተቋማትም ቀርባል።

ከዚያ በፊትም በ2004 በያመቱ የሚከበረውን ደመራ መነሻ በማድረግ በድህረ ገጾች ቀርቦ በሰፊው ቀርቦ ነበር። ከሃይማኖታዊው ይዘቱ ባሻገር አባቶች <u>የመደመር ጽንሰ ሀሳብ ለሀገር ክብርና ልዕልና</u> ለሩቅ ዘመናት <u>የተጠቀሙበት ግንዛቤ ለወጣቶች ተብራርቶ ባለመቅረቡና ፤ የዘመናችን ልሂቃንም የመደመርን ጽንሰ ሀሳብ በማወቅም ባለማወቅም እየናቁና እያጣጣሉ ከውጭ በወረሱት አፍራሽ ወጣቱን ግራ እያጋቡት ነው።</u> ምንም እንኳ የዘገየ ቢሆንም፤ በተከሰከሰባቸው መርዝ ጨርሰው ያላበዱት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ፋታ አግኝተው ቢመለከቱት፤ ወደፊት ለሚያደርጉት ብሄራዊ ግንባታ ይጠቅም ይሆናል በሚል ግምት ኢትዮጵያ በምትገለጽባቸው መስተጻምሮች ታጅቦ እንደገና ቀረበ።

ከኛ በፊት የነበሩት ሊቃውንት አባቶቻችን፡- ኢትዮጵያን የጠበቁበትን የመደመር ስልት በዘመኑ የምንገኝ ካህናት፤ በቃልም በተግባርም ለትውልዱ ባለማሳየታችን፤ ይልቁንም የግል ክብርና ድሎት አሳዳጆች ሆነን በመታየታችን፤ የቀደሙ ሊቃውንት አባቶቻችንና ቤተ ክርስቲያናችን ባዲሱ ትውልድ ሲነቀፉና ሲተቹ ስሰማ ይሰቀጥጠኛል።

በዚህ ዘመን ያሉ ልሂቃንም በቀደሙ አርበኞች አባቶቻችን ዘመን ነበረ የሚሉትን እንከን እያረሙ፤ ለኢትዮጵያ አንድነት በመደመር የተጠቀሙባቸውን <u>**ሁለገብ መስተጻምራት**</u> የበለጠ እያዳበሩ፤ እያራቀቁና የዜጎችንም ኅብረተ ሰባዊ ሁለንተና እጅግ ከፍ ባለ ስነ ህሊና

እንዲጣመር ማደረግ በተገባቸው ነበር። ኢትዮጵያ ከደረሰችበት ልዕልና ከፍ ማድረግ ባይችሉም እንኳ ከነበረችበት ታሪካዊ ልዕልና ዝቅ እንዳትል ከመታገል ይልቅ፤ **ብሔር ብሔር ሰቦች** በሚል መራኸ ቃላት፤ መደመርን በመስተጻምር እያጎላመሰ ኅብር የነበረውን ህብረተ ሰብ ከተጣመረባት መደመር እየፈለቀቁ ሲለያዩት ማየትና፤ ኢትዮጵያንም ከወጣቱ ስነ ህሊና ለማጥፋት የሚያደርጉትን ሸፍጥና ደባ መመልከት እጅግ ይዘገንነናል።

የውጭ ጠላት በየዘመናቱ በኢትዮጵያ ላይ የሚነስነስውን በታታኝ መርዝ፤ አባቶቻችን እየጠረጉ በትንቅንቅ ያቋረጡትን ዘመን ከዘመናችን፤ አባቶቻችን የነበሩባትን ዓለም እኛ ካለንበት ዓለማችን፤ የተጠቀሟቸውን የመደመር **መስተጻምራት፤** የዘመኑ ልሂቃን **"እስከ መገንጥል"** ከሚሉት አፍራሽ መርኋቸው ጋራ ወጣቱ እያነጻጸረ እንዲመረምረው እድል ቢያገኝ፤ ባላገሮች እያለ የሚነቅፉቸው አባቶቻችን ከዘመናችን ልሂቃን ይልቅ እጅግ የላቁና የረቀቁ እንደነበሩ በተረዳ ነበር።

በቅኝ ግዛት ስር ወድቃ በማታውቀው ኢትዮጵያ፤ ዜጎቿም ከጢሰኝነት ከተላቀቁ ከ40 ዘመን በኋላ፤ በቅኝ አገዛዝ ሥር በወድቁት አገሮች የተወለዱ እነ ጆሞ ኬንያታ አገራቸውን ከባእዳን ነጻ ለማውጣት የተጠቀሙበትን **"ብሔር ብሔር ሰቦች"** የሚለውን የዘማናችን ልሂቃን ኮርጀው፤ ኢትዮጵያዊውን ዜጋ **ተደምሮ ከተጣመረበት** ትስስር አላቀቁት። ኢትዮጵያንም ከዚህ አስከፊ ችግር ላይ ጣሏት። ወጣቱ ትውልድም እርስ በራሱ እንዲጠፋፋ አደረጉት።

ከታላላቅ ሊቃውንት አባቶቻችን አንዱ የሆኑት መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ባንድ ወቅት፡- *"ኢትዮጵያ በወራሪወች ያልተደፈረችባቸውን ዜጎቿም እርስ በርሳቸው የተጣመሩባቸውን መስተጻምራት ወጣቶቻችንን ሳናስተምራቸው ወደ ውጭ አገር መላክ፤ የኛን ምሳሌነት ማጥፋት ለሚፈልጉ ባእዳን፤ የፈለጋችሁትን ሙሉባቸው ብለን ባዶ ሸክላ መላካችንን አንዘንጋ። ሲመለሱ የሞሉባቸውን አተላ በኢትዮጵያ ይደፉባታል። ለመጥረግ በሚጥሩት ላይ የስራ ሸክም ማክበድ ይሆናል"* ብለው የተናገሩት ተፈጸመ።

ይህ አፍራሽና በታታኝ ስብከት ከ 1966 ቱ ትውልድ መንጭቶ፤ ለ27 አመታት በኢሀደግ ሲሰበክ ከኖረ በኋላ፤ በጠቅላይ ምኒስተር ዓቢይ አንደበት የተነገረችው **የመደመር** መርሆ፤ ተስፋ ሰጭ ብትሆንም፤ በቀደሙ አባቶቻንችን ስትገለጽ ከኖረችው መርሆ ጋራ ተጣምራ በተግባር ባለመተርጎሟ ልትጠቀም አልቻለችም። መደመር ልትጠቅም የምትችለው በትግህሶ፤ በመስተጻምርና በሌሎችም አንድምታወች፡- ማለትም በቅኔያችንና በብሔራዊ ስነ ልቡናችንና በ**ተግህሶ** ስትተረጎም ነበር። ተግህሶ ምን ማለት እንደሆነ እንመልከተው።

# ተግህሶ

**ተግህሶ** ማለት ከሚበክል ነገር ጋራ አለመደምር ማለት ነው። **ተግህሶ** ከትድምርት ጋራ በመነጻጸር ጎን ለጎን በጸሎት መጽሐፋችን ተደጋግመው ተገልጸዋል። ከከንፈራችን ርቆ ለማይሄደው ጻማ ከናፍር እንዳይሆን በጥንቃቄና በትኩረት እንድንረዳቸውና ፤ የዜግነታችን

መሰረት የሕይወታችን መመሪያ አድርገን ለህዝብ እንድናስተምራቸው የቀደሙ አባቶች አስተምረውናል።

በየዘመናቱ ከወደቁበት ተነስተው፤ ከተበተኑበት ተሰብስበው እንደመር ይሉ የነበሩት:- "ወእምኩሉ ምግባረ እኩይ **አግህሰነ**" ማለትም ከፉና ሸፍጠኛ ህሊና ካለው ሰው ጋራ አትደምረን ይሉ ነበር።

"ተግሀስ እመ እኩይ ወግበር ሠናየ" በምትለው ሐረግ ላይ የተመሰረተውን ሀሳብ በመጠቀም የተበላሸውን ከደህናው ጋራ ከመደመር ተጠንቀቅ። ለሰባዊ ፍላጎት ተቃራኒ፤ ለመለኮታዊ ህግና ትእዛዝ እንቅፋት ከሆነ ካልጸዳ ህሊና ጋራ፤ የጸዳ መስሎ ሊደመርህ ከሚሞክር ጋራ **አትደመር**። ይህን መመሪያ ከማይቀበሉ ከእኩያን ጋራ መደመር የሚያስከትለውን አደጋ "ጠብን እንዲያመጣ አውቀህ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርምር እራቅ "(2ኛ ጢሞ 2፡23)። ብሎ በሊቁ በገማልያል ጉባዔ በተቀረጸው በጳውሎስ ትምህርት በአጽንኦ ይናገሩታል።

"ወእምተደምሮ በዕልወት ወርኩስ ምስለ አላውያን ወአረማውያን (102፡85: _86) በሚል ምንባብም ተመርኩዘው፡ በእውነት ካልቆሙ ቃላቸውን በመቀያየር ህዝብ ከሚያወናብዱ ከከሀዲወችና ከጨካኝ አረማውያን ጋራ እንዳንደመር እርዳን" ማለት ነው። በጎ ህሊናን ከቆሸሸ ህሊና ጋራ መደመርን በ**አሻሮና** በቆሎ ድምር መስለው ይገልጹታል። ሸፍጠኞች አሻሮ ይዘህ ቆሎ ከያዘው ጋራ እንደመር ይላሉ። ቆሎ ከገለፈቱ የተላቀቀ የተበጠረ የጸዳ ነው። አሻሮ ከምርቁ ከገለባው ከገለፈቱ ሳይላቀቅ ታምሶ የቀረበ ነው። እኩያን ሰወች ንጹህን ህሊና ለማበላሸት፤ በኃጢአት ህሊናቸው ከታመሰና ተቆልቶ ካረረው ሀሳባቸው ሳይላቀቁ ከንጹሑ ጋራ በመደመር ስለሚበክሉት ተጠንቀቁ። ይሉ ነበር። እኛም ዛሬ እንላለን።

ከሸፍጠኞች ጋራ ላለመደመር:- የአህያ ሥጋን ከመብላት የሚገታንን ጽዩፍነታችንን እንድንጠቀም " ንህነሰ ናስቆርር ኩሎ ግብሮሙ ለዕልዋነ ሃይማኖት ወኩሎ ፍልጠተ ወዐሊወ ህግ እስመ ርኩሳን እሙንቱ በኀቤነ" (81 41) እያለ መጽሀፈ ቅዳሴያችን አጠንክሮና አጽንቶ ያስጠነቅቀናል።

አሻሮ ከገለፈቱ ሳይጠራ የታመሰ:- ግፈኞች ሰወች ከህዝብ ለሚዘርፉት ሀብት መግለጫ ነው። ግፈኞች ከህዝብ በሚዘርፉት ሀብት የከበሩና የሚዘልቁ መስለው ቢታዩም ፤ ጧት ታይታ ማታ እንደምትጠፋ እጸከንቱ ናቸውና "ኢትቅና ላዕለ እኩያን። ወኢትቅና ላዕለ ገበርተ አመጻ።እስመ ከመ ሳእር ፍጡነ ይየብሱ"(36፡1) ብሎ ዳዊት በተናገረው ስሜታችንን ቀርጸውት ነበር። ማለትም ከፉ ሰዎች በክፉ ስራቸው አብበው ለምልመው ብታያቸው እንደነሱ በሆንኩ ብለህ አትመኝ፤ ጊዜአዊ ኃይላቸውን እየተጠቀሙ ከህዝብ በሚዘርፉት አሻሮ ላይ በመሰረቱት ትእቢት እየተመኩ የሚፈጽሙትን ተድላና ደስታ አጥብቀህ ሸሸው። እንደሳር ፈጥነው ሲረግፉ ታያቸዋለህ። ይልቁንስ "ተግሀስ እመ እኩይ ወግበር ሠናየ"

እንደነዚህ ካሉት እኩያን እየሸሸህ የጎበጠውን ለማቅናት፤ የተጣመመውን ለማስተካከልና የጎረጎደውን ለመሙላት ከሚጥሩ በጎ ህሊና ካላቸው ዜጎች ጋራ **መደመርን** ተጠቀሙ።

# መደመር

ስለመደመር ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ምሳሌወች እየገለጸች መቼ፤ እንዴትና ለምን እንደተጠቀመችበት ያብነቱ መምህራን አባቶቻችን ባንድምታ ፈሊጣቸው ነግረውናል። በተግባርም እያደረጉ አሳይተውናል። ይህንንም በያመቱ ደጋግሜ ባቀረብኳቸው ጦማሮች ገልጫለሁ።

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን በሌሎች እንድትደነቅና በኢትዮጵያውያን ዘንድም ባለውለታ ከሚያደርጋት በደመር ከምትከውናቸው ቅርሶች አንዱ የደመራ በዓል ነው። የደመራን በዓል የጀመረችው እሌኒ የምትባለው ክርስቲያን ናት። የጀመረችበት ምክንያት የተሰወረውን የክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ነበር። በጀመረችበት አገር ዛሬ በታሪክ መዘገብ እንጅ በያመቱ እኛ በምናስታውስበት ሊታወስ ቀርቶ ተዘንግቷል። በቦታው የጀመሩት ክርስቲያኖችም ተበትነዋል።

የኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ከሃይማኖቱ ባሻገር ለሀገር ለወገን በሚጠቀም መንገድ በብዙ ምሳሌወች ስላስተማረችንና እኛ ልጆቿም እንደሌሎቹ ከሀገራችን ተነቅለን ስላልጠፋን ለራሳችንም ለኢትዮጵያም ህልውና ጋሻና መከታ እንዲሆነን አድርጋለች። በዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመደመር ኢትዮጵያን ከወራሪወቿ ካዳኗት ብዙ ቅርሶች አንዱ ሆኖ ተመዝግቧል። ካስተማረችባቸው ብዙ ምሳሌወች ያእቆብ ዘስሩግ (መ. ቅ. ገጽ 350፡ 68) እና ሌሎችም እንደ እነ ጎርጎርዮስ የመሳሰሉት ሊቃውንት እየደጋገሙ የጠቀሷት የምንቆርባት ህብስት ናት (መ. ቅ. ገጽ 373፡ 27_28)።

“ወበከመ አስተጋባእካ ለዛቲ ኅብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ውስተ አድባር ወአውግር ወታጋቢአ ኮነት አሐተ ኅብስተ ፍጽምተ ወከማሁ ኪያነሂ አስተጋብአነ በመለኮትከ እምኩሉ ሕሊን እኩይ፡ ውስተ ሃይማኖት” ብለዋል። ማለትም፡- ይህች ህብስት አካታ የያዘቻቸው የስንዴ ፍሬዎች፡- በተዘሩበት ወቅት በጎርፍና በማእበል ከመወሰድ፤ በቡቃያነታቸው ወቅት በቁጥቋጦ በእሾህ ከመታፈን ያዳንከ፤ አውድማ ላይ ወድቀው ሲበራዩ፤ ከገለባቸው ለይቶ ለሚያጠራቸው በታኝ ነፋስ ሲዘሩና ሲበተኑ፤ ተበትነው ከመጥፋት በአውድማው ሰብስበህ እንደገና ወደ ዱቄት ተለውጠው በውሀ ተለውሰው በእሳት ተዋህደው ወደ አንዲት ህብስትነት እንዲለወጡ ያደረከ፤ እኛንም ካለፍንባቸውና ከምናልፍባቸው ብዙ መከራና ስቃይ አድነህ ከዳኑት ጋራ ደምረን”

በሥጋቸውና በመንፈሳቸው በተግባራቸው እየተረጎሙ ያለፉት አባቶቻችን፤ በመከራ እየተፈተኑ ካለፉትና በማለፍ ላይ ካሉት ኢትዮጵያውያን ጋራ **መደመር** እንዳለብን ደጋግመው ነግረውናል። አቶ ለማ መገርሳ በሚቀያየር መሰረት በሊለው ሱስ መስለው ከተጠቀሷት

ኢትዮጵያዊነት ይልቅ፤ በደመነፍስ ጽምረት ረቃና መጥቃ በተደመረችው በማትቀየረው ነፍስ አባቶቻችን ይገልጿት ነበር።

በደመነፍስ ጽምረት ረቃና መጥቃ በተደመረችው ነፍስ የምትገለጸው ኢትዮጵያዊነት እንዳትደበዝዝ፤ በዓመት አንድ ጊዜ በምናስታውሰው የደመራ ብቻ ሳንወሰን በየሳምንቱ እሁድ "ደምረን ምስለ እለ ይድህኑ" እያልን ሊጦን በምንላት መጽሐፋችን በጸሎት መልክ እንድንደጋግማት አስተምረውናል።

# መደመር በመስተጻምር

አባቶቻችን መደመርን ከ ሀ እስከ ረ በተዘረዘሩት በአምስቱ መስተጻምራት ይተነትኗታል። አባቶቻችን **መስተጻምራት** ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነና እንዴትስ እንደተጠቀሙባቸው ለመግለጽ የቅኔውን ስልትና፤ በስልቱ ተጠናቅረው ኢትዮጵያውነት የሚንጸባረቁባቸውን ዘርፎች ከዚህ በታች ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## ክፍል 1 አምስቱ መስተጻምራት

**ሀ. ባለአገር፤**

**ለ. ባለጋራ፤**

**ሐ. ባለአምጣ፤**

**መ. ባለደም፤**

**ሠ. ባለቤት**

**ረ. ክልል**

## ክፍል 2 ኢትዮጵያዊት ቅኔ

**ሀ. ኮፌዳ፤**

**ለ. ውጥንቅጥ፤**

**ሐ. ሰምና ወርቅ፤**

**መ. ሰረዝ ፤**

**ሠ. ዓባይ**

## ክፍል 3 አርበኝነት

ከዚህ በላይ ቅርጻቸውን የዘረዘርኳቸው መስተጻምራት፤ ከዚህ በታችም ይዘታቸውን በመጠኑ ለማብራት እሞክራለሁ።

# ክፍል 1 አምስቱ መስተጻምራት

ከ ሀ እስከ ሠ የተዘረዘሩት **<u>አምስቱ መስተጻምራት፡-</u>** **<u>ባለ</u>** የምንላትን ሁለት ፊደላት መነሻ በማድረግ የህብረተ ሰቡን ስነ ህሊና ያጠናቀሩ ቃላት ናቸው። እነሱም፡- **አገር፤ ጋራ፤ ደም፤ አምጣና ቤት፤** ናቸው። **እነዚህ ቃላት** የኢትዮጵያን ህዝብ ህብርነት ውህደት፤ ሰምና ወርቅነትና ሰረዝነትን የሚያንጸባርቁ ናቸው። በነዚህ መንፈስ ከተጣመረው ኢትዮጵያዊ ኅብረተሰብ ማህጸን **<u>ባለአገርነት</u>** ተጸንሶ ይወለዳል። **<u>ባለ</u>** <u>አገር</u> ምን ማለት ነው?

## <u>ሀ. ባለ አገር</u>

አርበኝነትን ጸንሶ የሚወልደው **<u>ባለ</u>** <u>አገር</u> ምን ማለት ነው? በምዕራቡና በምሥራቁ ትምህርት ታዝሎ ወደኢትዮጵያ የገባው አባቶቻችን **<u>አተላ ያሉት</u>** nation nationalisim የተባለው ወራሪ ቃል የባለአገርን ትርጉም በኋላ ቀርነት ገልብጦ ኢትዮጵያውነትን ከወጣቱ ጭንቅላት አጥቦ እስኪያወጣው ድረስ፤ በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በተካተቱት ጎጆዎች፤ መንደሮች፤ አጥቢያወችና ወረዳወች የተወለደ ሁሉ ለመላ ኢትዮጵያ ሁለንተና **<u>ባለ አገር</u>** ነበር። ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር አገሩ ነበረች። የ**<u>ባለአገር</u>** ትርጉም ክብር፤ ኩራት፤ እንጅ ውርደት ስድብና ኋላቀርነት አልነበረም። ለመወሀድ ከምንቀባው ቅቤና ከምንልሰው ማር ይልቅ የኢትዮጵያን ዜጋ እንደ ሙጫ ሆና አጣምራና ደምራ የያዘችው <u>ባ**ለደም**ነቱ</u> ነበረች።

## <u>ለ. ባለ ደም</u>

**"እስመ ነፍስ ተሀድር በደም"(ዘሌ 17፡11)** እንዲል መጽሐፍ፡- ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንዱ ላንዱ **<u>ባለ ደም</u>** ነው። በሰውነታችን የሚመላለሰው ደም የነፍሳችን ዙፋን ነው። ደም ከሌለ ነፍስ የለም። ህልውናችን ደማችን ነው። **ባለደም** ማለት፡- **አንተ ለኔ የደሜ ባለቤት ነህ፤ እኔም ላንተ የደምህ ባለቤት ነኝ፤ ደምህን እጋራለሁ። ደምህ ደሜ፤ ደሜም ደምህ ነው። ህይወትህ ህይወቴ ነው። እኔ ያላንተ፡ አንተ ያለኔ፡ ህይወት የለንም ማለት ነው።** ይሁን እንጅ በሩቅ ዘመን ዳህጽ አተረጓጎም፤ ትርጉሙ መሰረቱን ለቆ በግድያ ወደ ሚፈላለጉ ወገኖች ተገልብጧል። ቀጥለን **<u>ባለጋራ</u>** የምትለውን ቃል እንመለከታለን።

## ሐ .<u>ባለጋራ</u>

**<u>ጋራ</u>** (አንድነት ወይም እኩል ) የምንላት በሁለት ፊደላት የተዋቀረች መስተጻምር የተለያዩ ስሞችንና ይዘት ያላቸውን አካላት በእኩልነት እያሰለፈች ለህልውናቸው የሚጠቅሟቸውን ነገሮች እኩል የሚካፈሉትን አካላት ታሳያለች። **"ጋራ"** የምትባለው ሁለት ፊደላት መስተጻምር **"ባለ"** የምንላትን አገናዛቢ ሁለት ፊደላት ተንተርሳ ወደ ህብረተ ሰብ ስትቀርብ፤ በክልል በጎሳ በቋንቋና በሃይማኖት ተሰንቅሮ በጎረጥና በከረረ ጥላቻ የሚተያይበትን መንፈስና ስሜ አፍርሳ፤ ኅብረተ ሰቡን በማይበጠስ ስነ ልቡናዊ ሰንሰለት አስተባብራ የምታስተሳስር ነበረች። **ጋራ** የምትለውን ቃል ለየተ ባለ አነጋገር ስንጠቀም ደግሞ **"አጋር"** ትሆናለች። አጋር ማለት፡- የሚረዳ የሚታደግ የሚያግዝ ዘመድ ወገን ማለት ነው።

**"አንተም ሰርተህ ብላ፤ አንችም ሰርተሽ ብይ፤**

**ያለ ኢጋር እንጀራ አይበላም ወይ" እንዲሉ።**

**"ባለ"** ከእለት ምግባችን ከእንጀራ ***ጋራ*** ስትጣመር **ባለእንጀራ** ትሆናለች። በወንፈል በደቦ በሀዘን በደስታ አብረው አድገው የደረሰባቸውን እያወቁ ለትውልዱ እያሻገሩ የሚያልፉ በሥጋ በደም የተሳሰሩ ማለት ነው። በመቀጠል የ**አንጣ** ወይም የ**አምጣን** አጠቃቀም እንመልከት።

## መ፡-አምጣ አንጣ፡-

ሰውነታችን ይመጋገባል፤ ይቀባበላል፤ ይረዳዳል፤ ይተጋገዛል፤ ይግባባል፤ ይዋዋሳል ይወሳሰዳል፤ ይበዳደራል፤ ያበደርኩሁ ያበደርከኝ፤ ያቀበልኩህ ያቀበልኸኝ፤ ያዋስኩህ ያዋስከኝ፤ የሰጠሁህ የሰጠኸኝ የምመልስልህ የምትመልስልኝ፤ የምታመጣልኝ የማመጣልህ **ባለ አምጣህ** ነኝ፤ **ባል አምጣየ** ነህ፤ በመባባል አንዱ ባንዱ ህሊና ውሥጥ ያለውን የወገንነትንና የዜግነትን መንፈስ ለመቀባበልና ለመወራረስ ይፈላለጋል ይሳሳባል። ይህም ማለት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ሁለንተና በእኩል **ባለቤት ነው።**

## ሠ፡- ባለ ቤት

**ባለ ቤት፡-** ቤት ሁለት ትርጉም አለው። ለመኖሪያ የሚሰራው ህንጻ ሲሆን፤ ሌላው በውስጡ የሚኖሩት ባለ ቤቶች (ባልና ሚስት) ናቸው። ጥምረታቸውን ለመግለጽ ወንዱ ለሴቷ ባለቤቷ ነው። ባለቤቴ ትለዋለች። ሴቷም ለባሏ ባለቤት ናት። ባለቤቴ ይላታል። ቤቱ ሁለቱንም አጣምሮ የእኩልነት ንብረት ነው። ከዚህ በላይ በዘዘርናቸው በባለ አገር፤ በባለ ጋራ፤ በባለ ደምና በባለ አምጣ ለሚነካካ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ኢትዮጵያ መኖሪያቸውና ማደሪያ ቤታቸው ናት።

ዘርፉ ቅጽሉና ምሳሌው ተሰማምቶ፤ ዜማውን ሳይሰብር፤ በማሰሪያ ግስ ህብር ተቀምሮ፤ በሚቃረን ሀሳብ (በፍርቅ ጸያፍ ሳይወላገድ) **ሳይካለል** የሚቀርብ አመርቂ ቅኔ ***ቤት መታ*** ይባላል። በኢትዮጵያ ያለው ህብረተ ሰብ እርስ በርሱ ሲጋባ፤ መንደር፤ ወረዳና አውራጃ ሰርጎ በመግባት ሲሰርግና ሲሰራረግ፤ አንዱ ባንዱ ሰውነት ሰርጎ ሲገባ ፤ "ውሔምኮ ውስተ ኩሉ ግብረ እደዊከ" እንዳለው ሁሉም እርስ በርሱ ተሰያየመ። ማለትም፡-አንዱ ካንዱ የተካለለበትን አጥር አፈረሰ ማለት ነው።

## ረ፡-ክልል

**ክልል** በዘመኑና በህብረተ ሰቡ ባህርይ መቀያየር ላይ ተመስርታ ዘመንና በዘመን ውሥጥ የተለያዩ ሚናወችን የሚጫወቱትን የሰዎችን ባሕርያት የምትገልጽ ቃል ናት። ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም" እያልን ከምድራዊ ቁስ ነገር በላይ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ልዑለ ባሕርይ እንገልጽባታለን። ዘመኑ ዘመነ ፍስህ ሲሆን የመከባበር የመፈቃቀር የሰባዊ **ክብር፤ ልዕልና፤ ሞገስና ግርማ** መግለጫ ትሆናለች። በዝብዝበዛ በሸፍጥ ሳይበከሉ ተልኳቸውን በተገቢው መንገድ የተወጡትን ወገኖችን ልዕለ አዕምሮ ለማሳየት "ክብረ ወስብሐተ **ከለልኮ ወሴምኮ** ውስተ ኩሉ ግብረ እደዊከ። መዝ 8፡1__9 እንዲል፡- መከበርን መወደድን መፈቀርን መወደስን ታንጸባርቃለች።

ዘመኑ ተቀይሮ እንዳሁኑ ዘመነመንሱት ሲሆን፤ ሰወች ሰባዊና ብሄራዊነታቸውን ሲስቱ **ክልል** ትርጉሟን ቀይራ “ሕቀ አህጸጽኮ” እንዲል፡- መጉደለን፤ መዋረድን ማነስን፤ መቀነስን፤ መካለለን፤ መወጋገድን፤ መቆራረጥን፤ መለያየትን ታመለክታለች።

በኢትዮጵያዊት ቅኔ ህሊናቸው የከበረላቸው ጀግኖች፤ ኅብረተ ሰቡን አጥሮና ቀይዶ የያዘውን ክልል ደርምሰው፤ የተገራረደበትን ጥቁር መጋረጃ ቀዳደው ፤ በ**<u>ኢትዮጵያዊት ቅኔ</u>** መፈክራቸውን እያሰሙ ካያሉበት ጎራ ይወጣሉ።

## <u>ክፍል 2 ኢትዮጵያዊት ቅኔ</u>

**የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ስለምንምንገልጽባት ስለ ኢትዮጵያዊት ቅኔ ስናስብ ከብዙ ዓይነት ቅኔወቻችን ጥቂቶችን ማለትም፡- ኮፌዳን፤ ውጥንቅጥን፤ ሰምናወርቅን፤ ሰረዝንና ኅብርን ብቻ ለመመልከት በኮፋዳ እንጀምራለን።**

### <u>ሀ. ኮፌዳ</u>

በመስተጻምራቱ አማካይነት ኢትዮጵያን በደመ ፍሳችን እንድትቀረጽ ወዳደረገችው **<u>ኢትዮጵያዊት ቅኔ</u>**ያች ለመሻገር በ**<u>ኮፌዳ</u>**ችን እጀምራለሁ። ኮፌዳ ከሰሌን ወይም ከቄጠማ የምንሰራት በየመንደሩ እየዞርን በመለመን የምንሰበሰበውን ምግብ ለመያዝ የምታገለግለን ዕቃ ናት። ከህብረተ ሰቡ የምንሰበስበው ልዩ ልዩ ምግብ ወደ ኮፌዳችን ሲገባ ስሙን ለወጥን **ውጥንቅጥ** እንለዋለን። በቅኔ ትምህርታችን ኮፎዳችንን **<u>ሰም</u>** ኢትዮጵያን **<u>ወርቅ</u>** እናደርጋታለን። ከህዝቡ የምንሰበስበውን **ውጥንቅጥ** ህዝብ ገላጭ ሰም እያደረግን፤ በቋንቋና በሃይማኖት ተወናቅጦ በጠረፏ ክበብ ሰብስባ የያዘችውን አገራችን ኢትዮጵያን ወርቅ እያደረግን እንቀኛለን። በሰምነት የምታገለግለን ኮፌዳችን ብትቀደድ **ውጥንቅጣችን** ስለሚፈሰብን እንዳትቀደድ እንጠነቀቅላታለን።

ህዝባችንን ሰብስባ የያዘችው ኢትዮጵያም ዳር ድንበሯ ቢደፈርና ቢገሰስ እኛነታችን ስለሚበታተን፤ ዳር ድንበሯ እንዳይደፈር ነቅተን የመጠበቅ ብሄራዊ ግዴታ፤ እዳና ፍዳ ከመከፈል እንዳንሸሽ ኮፌዳችን እንዳትቀደድብን የምናደርገውን ጥንቃቄ በኢትዮጵያ ዳር ድንበር እየመሰልን እንቀኛለን።

የኢትዮጵያን ድንበር ወርቅ፤ ኮፌዳችንን ሰም፤ ከህዝቡ የምንሰበስበውን ምግብ ( **<u>ውጥንቅጥ)</u>** ሰም፤ በሥጋ በደም የተወናቀጠውን ህብረተ ሰባችን ወርቅ እያደረግን በምንማረው ኢትዮጵያዊት ቅኔ፤ ኮፌዳችንና በኮፌዳችን የምንስበስበው የተደበላለቀው ምግብ ለጠለቀውና ለረቀቀው ቅኔያችን መነሻ ፊደሎች ናቸው። ውጥንቅጥ ሌላም ጽንሰ ሀሳብ አላት።

### <u>ለ. ውጥንቅጥ</u>

**<u>ውጥንቅጥ</u>** ተጨማሪ ባህርይ ገላጭ ትርጉም አላት። ቃሏን ሰንጠቀን በሁለት መንገድ እንጠቀምባታለን። **<u>ውጥን</u>** (ጅምር) እና **<u>ቅጥ</u>** (ቅርጽ) ብለን እንሰነጥቃታለን። **<u>ውጥን</u>**

የምትባለውን ቃል **<u>ቅጥ</u>** ለምትባለው ቃል ገላጭ ቅጽል በማድረግ፤ እንዳይነብጥና እንዳይወላገድ ሆኖ በኢትዮጵያዊት ቅኔ ስነ ልቡናው የተወጠነ ኢትዮጵያዊ ማለት እንደሆነ አስረድተውናል። ለቅኔያችን መሰረት ከሆኑት መጻህፍት ብዙ ማስረጃወች ይጠቅሳሉ። ከሚጠቅሷቸው መጻህፍት አንዱ የሰሎሞን መጽሐፍ ነው።

"ልቡ ለራጎ ከመ መንኮራኩረ ሠረገላ ወከመ መንኮኮት እንተ ተዐውድ" (ሲራ 36፡5) ብሎ በተናገረው ምሳሌያዊ ንግግር ይገልጹታል። ይህም ማለት፡-የበለጠ ስትብራራ የሚፈራ ሰው የተረጋጋ ስነ ህሊና የለውም። በፍርሀትና በጥርጥር እንደ ሰረገላ ሞተር ይሽከረከራል። ፈታይ ሴት እንደምታሽከረክራት እንዝርትም ይሾራል። ኢትዮጵያ ከፈተና በምትወድቅበት ዘመን ይህን የመሰለ አረግራጊና ተሽከርካሪ ባህርይ ያለው ቀጥ ብሎ ይቆማል ተብሎ አይታመንም ብለውም ነግረውናል።

## ሐ. ሰምና ወርቅ

በሰምና በወርቅ የሚቀመረው ቅኔ የሚያስደንቅ አገላለጽ አለው። ምን ማለት እንደሆነ ባጭሩ እንመልከት። የሁለቱ ማለትም የወርቅና የሰም ባህርያት የተላያዩ ናቸው። ወርቅ የማይለወጥ የማይዝግና ዘላቂነት ባህርይ አለው። ሰም ግን በቀላጭነት ባህርይዋ ለወርቁ ቅርጽና ይዘት ትለቃለች እንጅ ከወርቁ ጋራ አብራ አትዘልቅም። በሰምና በወርቅ ቅኔ ህብረተ ሰብን ከመግለጽ ተጠንቀቁ ይላሉ። በተጨማሪ ሲያብራሩ ሰም ከወርቅ ጋራ **ዕሪና** (equilibrium) ስለሌላት የህብረተ ሰብ መግለጫ ሆና አታገለግልም። ሰውና ሰውን ለምገለጽ ሰምና ወርቅ ቅኔ የምትጠቀሙ ከሆነ አንዱን ቀላጭ ሰም ፤ ሌላውን አቅላጭ ወርቅ ማድረግ ስለሆነ ተጠንቀቁ ይላሉ። እኔ ወርቅነኝ እያለ በህዝብ ፊት ቆሞ የሚናገር ራሱን አቅላጭ፤ ሌላውን ቀላጭ ማድረግ ስለሆነ ፍርቅ ጸያፍ ነው ይሉናል። ከዚህ ቀጥየ ይዘቷ ከሰምና ወርቅ በመስፋት ኢትዮጵያውነታችንን <u>በድርብርብ</u> መንፈስ ስለምትገልጸው **<u>ሰረዝ</u>** ስለምታበለው ቅኔ ትንሽ መግለጽ ጠቃሚ ይመስለኛል።

## <u>መ. ሰረዝ</u>

በዚህች ቅኔ የበህረተሰቡን በሥጋ በደም ድርብርብነት እንማርባታለን። ሰረዝ ቅኔ በድርብርብ ባህርይዋ ድርብርብ አካል ባላት በቀይ ሽንኩርትና፤ ድርብርብ ጥርስ ባላው በብረት ሞረድ ትመሰላለች። ጥርሱ ሲረግፍ ድድ ብቻ ሲሆን እየተወቀረ እንደገና አዲስ ጥርስ በማውጣት ብረት በሚስልና ጠጣር ጥራጥሬ በሚፈጭ የድንጋይ አይነትም ትመሰላለች። በዚህ የይዘት አቅሟ ብዙ የደራረቡ ወርቆችንና ብዙ ሰሞችን ደራርባ ስለምትይዝ ከመደበኛው ሰምና ወርቅ ቅኔ በይዘቷ ትሰፋለች። የተደራረቡትን ሰሞችናንና ወርቆችን በቅጽሎች እና በማሰሪያ ግሶች በዕሪና (equilibrium) ህብር እያደረገች አምስቱን መስተጻምራት አጉልታና አራቃ የያዘች ናት።

አንድ ኢትዮጵያዊ ከአራት አቅጣጫወች በወረሰው ሥጋውና ደሙ ሰረዝ ነው። በአባቱ በኩሉ ከሴትና ወንድ አያቶቹ፤ በናቱም በኩል እንደዚሁ ሴትና ወንድ አያቶቹ ማለትም ካራቱ አያቶቹ አጠናቅሮ በተሸከመው እሱነቱ ሰረዝ ነው። ቢያንስ ከአራት

ድርብርብ ቤተ ሰቦች በተሸከመው ደም ግባት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መላ ኢትዮጵያውያንን **ኅብር** የሚያደርግ ሰረዛዊ ቅኔ ነው።

ባለአገሮች አባቶቻን ይህችን ሰረዛዊት ጽንሰ ሐሳብ መሰረት በማድረግ በሃይማኖት በቋንቋና በገጸ ምድር  እንዳንለያይና  እንዳንከፋፈል፤ ይልቁንም እንድንሞራረድ እንድንሳሳል አስተምረውናል። በዚህች ቅኔ ሊቃውንቱ ሳይወቀሩትና ሳይሳሉት ዳዊት በመድገም ብቻ የቄስ ተማሪ ነበርኩ ብሎ ማውራት ቅኔዋን ማርከስ፤ ሊቃውንቱን ማሳነስ ነውና ተገቢ አይደለም ይላሉ አባቶች። ኅብር እና ሰረዝ በጥቂቱ የመወራረስ ባህርያት አሏቸው። በተለይ ህብር ለጠቅላላ ዜግነታችን መገለጫ ስለሆነችና “ብሄር ብሄረ ሰቦች” በሚል መርሆ ህዝባችን በተበታተንበት ወቅት ብንመለከታት ያባቶቻችንን ጥበብ ለማወቅ ስለምትረዳን ከዚህ በታች ህብር የምትባለውን እንመልከታት።

## ሡ. ኅብር

ኢትዮጵያዊ ሁሉ እርስ በርሱ **ኅብሬ** ነህ መባባሉን ስለሚያፈርስበት፤ ብሄር ብሄረሰቦች የሚለውን ከፋፋይ እኩይ ዘዴ ኢትዮጵያዊት ቅኔያችን አትቀበለውም። አባቶቻችን ኢትዮጵያዊት ኅብርነታችንን በብዙ ምሳሌዎች ይገልጿታል።  ከብዙ ምሳሌዎች አንዷ ነቢዩ ኤርምያስ “ነብር ዝጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ መልኩን ይቀይራልን?”  (ኤርምያስ 13፡23) ብሎ የተናገራትን ናት።

በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፤ ባንድ ነብር ሰውነት ላይ ያሉትን ነጠብጣቦች ይወክላሉ። በቦታ የተለያዩ ነጠብጣቦችን የተሸከመው የነብሩ አንድ አካል፤ በወረዳና ባውራጅ ተለያይተው ያሉት ጎሳዎችን የተሸከመችውን አንዲት ኢትዮጵያ ይወክላል። ህብሮች ኅብርነታቸውን ሳይቀይሩ ሳይጠፋፉ የነብሩን አካል እያደመቁ እንደሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ባህርያቸውን ሳይቀይሩ የተበታተነ ማንነታቸውን ባንዲት ኢትዮጵያ ኅብር ያደርጋሉ።

ነቢዩ ኤርምያስ ኢትዮጵያዊ ስነ ሕሊናችንን ከማይቀየረው ከነብር ዝጉርጉነት ጋራ አነጻጽሮ በጥያቄ የገለጸው፤ እራሱ ኤርምያስ ነጻነቱን ተገፎ ሰባዊ ክብሩን ተዘርፎ እመቀ እመቃት በወደቀበት ወቅት፤ አቤሜሌክ የሚባል ሰው  (ኢትዮጵያዊ)  በገመድ ጎትቶ ከወደቀበት ጉርጓድ አውጥቶታል።  መምህሮቻችን ኤርምያስ ከተወረወረበት ጉድጔድ ተጎትቶ የወጣባትን ገመድ  ለማትበጠሰው ርበኛነታችን  መግለጫ እያደረጉ አስተምረውናል።

አቤሜሌክ  “በእኔ ስለታመንክ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም። አድንሀለሁ። ነፍስህም እንደምርኮ ትሆናለች እንጂ አትወድቅም” (38፡13) የሚል ጿጋና በረከት በአርበኛነቱ እንደተጎናጸፈባት፤ ኢትዮጵያውንም  በፈጣሪያቸውና በረሳቸው ጽኑ እምነት ላይ የተመሰረተችው አርበኛነታቸው በጠላት ላይ ድል የመቀዳጀት ጿጋና በረከት ይጎናጸፉባትል እያልን እንድንቀኝ አስተምረውናል። **በቅኔ ትምህርታችን የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ከምንቃኝባቸው አንዷና ዋናዋ በእምቦጭ የተወረረችው የዓባይ ወንዛችን ናት።**

## ፈ. ዓባይ

**በመስተጻምራቱ** አማካይነት ኢትዮጵያን በደመ ፍሳችን እንድትቀረጽ ያደረገች የቅኔያችን መሰረት **ኮፌዳ**ችን እንደነበረች ተመልከተን ነበር። አሁን ደግሞ ከኮፌዳችን ጋራ እያነጻጸርን የኢትዮጵያዊነታችንን ጥንቅር የምትገልጸውን **ዓባይ**ን እንመለከታለን።

ዓባይ በኢትዮጵያ አካል የሚፈሱትን የአፍላጋት ክምችት (ገባር ወንዞች) እየሰበሰበች አስተባብራ በመያዟ፤ ከየመንደሩ የምንሰበስበውን ውጥንቅጥ ሰብስባ ከምትይዘው ከኮፌዳችን ጋራ እያነጻጸርን በሰምናወርቅ፤ በሰርዝና በህብር እንቀኝባታለን።

በዓባይ አማካይነት ቅድስት ኢትዮጵያ አገራችን፤ ለኛ ለኢትዮጵያውያን እናትነትን ካገርነት ጋራ አጣምራ የያዘች ወላጅ እናታችን ናት። ለግብጾች የእንጀራ እናታቸው ናት። የሚፈሱትን አፍላጋት (ገባር ወንዞች) ሰብስባ በእናት ኢትዮጵያችን አካል የምትፈሰውን የዓባይ መፈለቂያ ምንጭ ግሼ ዓባይን የኢትዮጵያ ልብ ናት እያልን እንቀኛለን።

"ወእንዘ በርስእ ሀለወት፡ ኲሎ ተሐድስ፡ ወበበ ትውልድ ምስለ ነፍሰ ጻድቃን ትትፋለስ" እንዲል፡- ዓባይ ጥንታዊት ስትሆን የማታረጅ የስነ ልቡናችንን ቅኔ ሰንቃ በየትውልዱ አካል በመፍሰስ ትውልዱን ሁሉ እያደሰች እንደምትኖር ተምረንባት ነበር። ለምለሚቷ ኢትዮጵያ እናታችን ከማህጸኗ የፈለቁትን እንደ አጼ ቴወድሮስ፤ እንደ በላይ ዘለቀ የመሳሰሉትን ጀግኖች፤ እንደነ መላከብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የመሳሰሉት ሊቃውንት እያጠጣች ያሳደገችበት ውሀ፤ በተፈጥሮ እኳለ ማውታነታቸው የነጻነት ድርቅ ያጠቃቸውን ሱዳናውያንንም ግብጻውያንንም ጠጥተው እንዲረኩ **"ኑ ! የነጻነትን ውሀ ከኔ እየጠጣችሁ እርኩ"** እያለች ስትጋብዝ ኖራለች ።

# ክፍል 3 አርበኝነት

አርበኛ ከማይደርቀውና ከማይነጥፈው ህብረተ ሰብ ማህጸንና አብራክ በመከራ ጊዜ የሚመነጭ ለኢትዮጵያ ዘበኛና ቤዛ ሊሆን ከየመንደሩ የሚወልድ ቡድን ነው። ቃሉ አኀዛዊ ለዛና ትርጉም አለው። ይሁን እንጅ ህብረተ ሰባችን በሩቅ ዘመን ዳህጸ ልሳኑ **40ኛ** የሚለውን አኀዛዊ ቃል ወደ ልሙጥነት ቀይሮ **አርበኛ** ይለዋል። ለረዥም ዘመን በቅኝ ገዥዎች ያልተገዛ ኢትዮጵያውያንን የመሰለ ህዝብ ባንድ ወቅት የጀመረውን ነገር ጽንሰ ሀሳቡን ሳይረሳ፤ ስም አጠራሩን በዳህጸ ልሳን እየቀየረ ለትውልድ ማቀበሉ የተረጋገጠ ነው።

ለምሳሌ ኢትዮጵያን ጦቢያ፤ ነነዌ የሚለውን **ነይነይ** እያለ አጠራራቸውን በመቀየር እንደሚጠራቸው ማለት ነው። እንደዚህ ሁሉ ህብረተሰባችን **40ኛ** የምትለውን አኀዝ ወደ ፊደለኛ አነጋገር በመለወጥ በልማዳዊ ዳህጸልሳን **አርበኛ** እንደሚላት ያብነት መምህራን ነግረውናል። የ**40ኛን** ስርጸት እንዴት እንደሚገልጿት ከዚህ በታች እንመልከት!

ያንድምታው መምህሮቻችን የ**40ኛነት** ስርጸት ለመረዳት በዮቶርና በሙሴ መካከል የነበረውን የማቀበልና የመቀበልን ጸጋ ተመልከቱ ይላሉ "ስምአኒ እንዘ እመክረከ

ወእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ ወኩኖሙ ለህዝብ ወለእግዚአብሔር ወትበትክ ቃሎሙ ”

(ዘጽ 18፡19) ብሎ ዮቶር ለሙሴ የሰጠውን ምክርና ጥበብ ተቀብሎ፤ እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት ሙሴ በአርበኝነት ስሜትና መንፈስ ተንቀሳቀሰ። “ወአመ ተፈጸመ **አርባ አመት** ሐለየ በልቡ የሐውጾሙ ለአኀዊኑ (የሐዋ 7፡ 23)። እንዲል፡- ማለትም፡-የዮቶርን ምክር የሰማው ሙሴ 40ኛው አመት በተፈጸመ ጊዜ ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት ልቡ ተነሳ። አባቶቻችን ከዚህ በመነሳት **40** ዘመንን ሰው ቁም ነገር ለሚሰራበት እድሜው ማእከል ናት ይላሉ።

ህይወቱን በትግል ጀምሮ በንስሀ የፈጸመው ዳዊትም “እመሰ በዝኃ ሰማንያ ዓም ወፈድፋዶንሰ እምእላ ጻማ ወህማም” (መዝ 89፡9) ብሎ በተናገራት ሐረግ፤ አባቶቻችን የ**አርበኛን** ጽንሰ ሀሳብ አጠናክረዋታል። ይህም ማለት፡-ሰው በዚህ ዓለም የቆይታ ዘመኑ ግፋ ቢል ሰማንያ ነው። ሰውነቱ ሳይከብደው፤ ወገቡ ሳይያዝ፤ ቋንጃው ሳይቀየድ፤ ጉልበቱ ሳይደነዝዝ፤ አእምሮው ሳይፈዝ፤ ህሊናው ሳይነፍዝ አቀበት ወጥቶ ቁልቁለት ወርዶ የፈለገውን መፈጸም የሚችለው እስከ **80** ዘመኑ ነው። ሰው የፈለገውን የሚፈጽምባት አፍላ ዘመኑ የ**80** ዘመኑ ማእከል የሆነችው **40**ኛዋ ዕድሜ ናት።

የአርባኛነትን ጥንቅር በትኩረት እንመልከታት። **ባ** የተባለችው ፊደል **በ** ሆና አርባኛን በመቀየር **አርበኛ** ታሰኛታለች እንጅ **አርባኛ (40ኛ)** ማለት አኀዝ ነው። ነፍጠኛ የምትለውን ቅጽል የተረዳንባት **ኛ** የምንላት ፊደል ለአኀዝ ትራስ በመሆን ወደ መግለጫ ቅጽልነት እንደተቀየረች ማለት ነው። ለምሳሌ፡- ፈረስ በሚለው ላይ **ኛ** ስትደመር ፈረሰኛ፤ በአንድ፤ በሁለት፤ በአስር ቁጥሮች ላይ **ኛ** ትራስ ሆና ስትደመር ወደ ገላጭ ቅጽልነት ይለወጣሉ። እንደዚሁም **ኛ** በ **40** ቁጥር ላይ ትራስ ሆና በመደመር **40ን** የአኀዝነትን ትርጉም ሳታስለቅቅ ግብር ገላጭ ቅጽል ታደርጋታለች።

አባቶች ሊቃውንት እንደሚሉት፡- በሀገር ላይ ዜጋን የሚፈትን ጠላት ሲከሰት 40ኛ ይጠራራል። **40ኛ** (አርበኛ) የሠራዊት እፐረት ቢገጥመው ከራሱ 40ኛ ዕድሜ ዝቅ ወይም ከፍ ያለ ፋኖ (ወዶ ዘማች) በጥንቃቄ ይመለምላል። ይህም ማለት በጦር ሜዳ የሚሰለፍ ከ20 እስከ **60** ባለው እድሜ ክልል ያለ ዜጋ ነው። ከ20 አመት እድሜ በታች ያሉት ወጣቶች እንዲሰለፍ አይገፋፉም፤ ከ60 በላይ ያሉ አዛውንቶች እንዲዘምቱ አይደግፉም።

ከ20 አመት እድሜ በታች ያለ ወጣት በግንባር ቀደም ለጦርነት እንዲሰለፍ የማይገፋፉት በእሳታዊ ባህርዩ ፈጥኖ በመገስገስ በሚወስደው ርምጃ በጥንቃቄና በጥናት ተዘጋጅቶ ለመጣ ጠላት እንዳይጋለጥ ሊጠነቀቁለት እንጅ፤ በፍታውራሪ ተክለ ሐዋርያት እንደተገለጸው ፤ ከ20 እድሜ በታች ባለው ወጣት ውስጥ ያለውን ኃይል ዘንግተውት አይደለም።

የአለቃ ገ/ ዮሐንስ የቅኔ ተማሪ የነበሩት ታላቁ አባታችን ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በአድዋው ጦርነት ጊዜ የተፈጸመውን ትዝታ ባሰፈሩበት መጽሐፋቸው ከገጽ 55 እስከ 76

ላይ እንደምናነበው፤ ከ20 እድሜ በታች ያሉ ወጣቶች በግንባር ተሰልፈው ከሚዋጉት 40ኞች ጋራ ተቀላቅለው በመዋጋት ላይ ሳሉ፤ 40ኞች ለይተው ከጦር ሜዳ በማውጣት ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ተቆጥተው ቢሸኟቸም፤ እንደገና እየተደበቁ ወደ ጦርነቱ ሜዳ በመቀላቀል ታላቁን ጀብዱ እንደፈጸሙ ነግረውናል።

በደማቸው ውስጥ በሰረጸችው በአርበኛነት ስሜት የዜግነታቸውን ኃላፊነት እየተወጡ ያለፉት የዘመናችን ልሂቃን ባለገሮች እያሉ የሚንቋቸው አርባኞች አባቶቻችን፤ ወራሪዎችን ተዋግተው በማሸነፍ ድል የተቀዳጁባቸውን መሳሪያወች፤ የተሸለሚቸውን ለምድ፤ ቀሚስና ካባ እንደ ሌሎች ቆሳቁስ በሥጋ ለወለዷቸው አላወረሱም። እስከ ዓለም ፍጻሜ በምድር ላይ በምትቆየው በቤተ ክርስቲያናቸው እቃ ግምጃ ቤቶቻችን እንዲቀመጡ ያደረጉት፤ በየዘመናቱ የሚኖሩት ካህናት በየዘመናቸው ላለው ትውልድ፤ አባቶቻቸው ኢትዮጵያን ጠብቀው ያቆዩባቸውን **መስተጻምራት** የማይዘነጉ ቅርሶች መሆናቸውን እንዲመሰከሩ ነበር።

ደመራ ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር ለህብረተ ሰባዊ ትድምርትና ጥምረት አባቶቻችን ተጠቅመውበታል። በኢትዮጵያዊትም ቅኔ፤ ኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቡና ከኢትዮጵያዊነት ጋራ በማጣመር ለሀገር ክብርና ልዕልና መሰረት አድርገዋት ነበር። ይሁን እንጅ የዘመናችን ልሂቃን ከውጭ በወረሱት አፍራሽ ለሀገር ክብርና ልዕልና መሰረት የነበረውን በማወቅም ባለማወቅም እየናቁና እያጣጣሉ አፈራረሱት። ኢትዮጵያዊነትንም ከወጣቱ ስነ ልቡና አውጥተው በመጣል ለኢትዮጵያዊነቱ ባእድ አደረጉት። እርስ በርሱም የሚያጋድል ደባ ሰሩበት። ምንም እንኳ የዘገየ ቢሆንም፤ በተከሰከሰባቸው መርዝ ጨርሰው ያላበዱት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ፋታ አግኝተው ይህችን ጦማር ቢመለከቷት፤ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ግንባታ አስተዋጽኦ መፈንጠቅ የሚያስችል ሀሳብ ይጭርባቸው ይሆናል ብየ ስለገመትኩ፤ ሊቃውንት አበው መደመርን አብራርተው የሚተረጉሙባቸውን መስተጻምራትንና የቀሩትን ከመደመር ጋራ የተያያዙትን ያንድምታ ዘርፎች አቀረብኩላችሁ።

ስለዚህ እናንት ልሂቃን ነን የምትሉ ወገኖች ሆይ! “ብሄር ብሄረ ሰቦች” በሚል ፈጠራ የወጣቱን ጭንቅላት እያዞራችሁ፤ እርስ በርሱ እንዲጠፋፋና ኢትዮጵያንም እንዲበታትናት የማድረግ ደባችሁን አቁሙ! ይልቅስ በዚያ ፋንታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን በመደመር ኅብር እንድንሆን የተጠቀመችባቸውን **ሁለገብ መስተጻምራት** ለማስተማር ብትጥሩ፤ አገራችን በባቶቻችን ዘመን ከነበራት ምሳሌነቷ እጅግ በተሻለና በላቀ መፍለቅለቅ የምሥራቋ ኮከበጽባህ ማድረግ ትችላላችሁ። ኢትዮጵያዊነትን በሚቃረን እኩይ መርኄችሁ ብትቀጥሉ ግን ልታጠፏት ከተሰለፋችሁባት ከኢትዮጵያ ጥፋት በፊት እራሳችሁ ትጠፋላችሁ ።

ያባቶቻችን አምላክ፤ ዓይነ ልቡናችንን ያብራልን !